

# የአሸንድዬ ባህላዊ ጨዋታ

## በላስታ ላሊበላ

## ነሐሴ ፳፻፬/2004







ላሊበላ
ነሐሴ ፳፻፬/2004

www.ethiopianorthodox.org

# 12. የዛግዌ ዘመን ሥነ-ጥበብ

ጌታቸው መረሳ(በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የአርኬዎሎጂና የቅርስ ትምህርት ክፍል
መምህር)

ክርስትና በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ እምነት ብቻ ሳይሆን በርካታ ሀገር በቀል ዕውቀት የፈለቀበትና የተካበተበት መድበለ ጥበብ ነው:: የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን ጀምሮም ኾነ ከዚያ በፊት ኢትዮጵያን በዓለም ደረጃ ልዩ ሥፍራ ያሠጧት ድንቅ የሥነ ጥበብ ሥራዎች ተፈጥረዋል፤ ዋና ዋናዎቹም ሥነ ሕንፃ (architecture)፣ ሥነ ጽሑፍ (literature) እና ሥነ ሥዕል (art) ናቸው:: እነዚህ የሥነ ጥበብ ውጤቶች ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪቃ አገሮች የራሷ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ያላት ብቸኛ አገር አድርጓታል፤ ድንቅ ውበት የተላበሱት ሐውልቶቿ፣ ሕንፃዎቿና ሥነ ጥበቧ ደግሞ ዓለምን ከማስደመም አልፈው ኢትዮጵያን በአንድ ወቅት ከሥልጣኔ ማማ ላይ ያደረሱ ነበሩ:: ይህ ጽሑፍ በዛግዌ ዘመን የታዩ ዓበይት የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ማለትም ሥነ ሥዕልን፣ የመስቀል ሥራንና ሥነ ጽሑፍን በቅደም ተከተል ይቃኛል::

የዛግዌ ዘመን ሥነ ሥዕል በዘርፉ ለተሠማሩ ምሁራን ዋነኛ የጥናትና ምርምር መስክ በመሆን የበርካታ አጥኚዎችን ቀልብ ስቦ ይገኛል:: የዘመኑን የሥነ ሥዕል ጥበብ በጥልቀት ከማየታችን በፊት ጥበቡ የተቃኘበትን ዐውድ ለመረዳት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥዕል አሳሳልና መለያ ባሕርያቱን (formal characteristics) ማየቱ ጠቃሚ ይኾናል::

የመጀመርያው ባሕርይ ሥዕሎቹ ምንም ዐይነት እንቅስቃሴ የማይታይባቸው (rigidity or lack of movement) እና ኢትዮጵያውያን ሠዓሊዎች እንዲህ ዐይነት የአሣሣል ዘይቤ ለመከተል ፍላጎት ያልነበራቸው መኾኑ ነው :: አልፎ አልፎ ይህ ዐይነቱ የአሣሣል ዘይቤ ማለትም እንቅስቃሴ (movement) የዐይታ አቅጣጫን (direction of an eye ) በመከተል ሥዕሉ ላይ የተወከለው ወንድ ወይም ሴት ወዴት እየተመለከተ እንደኾነ ለማሳየት ይሞክራሉ:: ሁለተኛው ባሕርይ፥ ከሌሎች በተለየ ሑኔታ ለሰው ምስል የተለየ ትኩረት መስጠት ነው:: እስከ 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ሠዓሊዎች በሥራቸው ውስጥ አካባቢንና የቤት ቁሳቁሶችን አያካትቱም ነበር:: ይህ ዐይነቱ የአሣሣል ዘይቤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትም በተለይም በባዛንታይን ዘመን የታየ ነው :: ከ18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን አልፎ አልፎም ቢሆን አንዳንድ የቤት ቁሳቁሶችን ማካታት ተጀምሯል:: ይህም የኢየሱሳውያን (Jesuits) ወደ አገራችን መምጣት ያስከተለው ተጽዕኖ ነው ተብሎ ይገመታል::

ሌላው የአሣሣል ዘይቤ ለዐይን የተለየ ትኩረት መስጠት ነው፤ ዐይን ሲሣል ምጣኔው የተለያየ (disproportional ) ተደርጎ ነው:: ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለተመልካቹ አክብሮት መስጠትን ፣ ቀናነትና ትኩረት መስጠትን ለማመልከት ነው:: ይህም ከባዛንታይን ዘመን የአሳሳል ዘይቤ ጋር ይመሳሰላል:: አራተኛው አቋቋም (pose) ነው፥ ኢትዮጵያውያን ሠዓሊዎች ሦስት ዐይነት የአቋቋም ዐይነቶች ይጠቀማሉ ፤ እኒህም ፊት ለፊት (frontal pose) ፣ የጎንዮሽ (profile) እና አንደኛው ጆሮ ብቻ እንዲታይ አድርጎ በ2/3ኛ ገጽታ መሳል (2/3 or one ear miss) ናቸው::

የፊት ለፊት የአቋቋም ዘይቤ ብዙ ጊዜ የሚዘወተርና በዚህ ዐይነቱ መንገድ የሚሣሉት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቅድስት ድንግል ማርያምና የሌሎች ቅዱሳን ፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ሥዕሎች ናቸው :: 2/3ኛ ወይም አንድ ጆሮ ብቻ እንዲታይ ተደርጎ የሚሣለው የአሣሣል ዘይቤም ከላይ ለተጠቀሱት ቅዱሳን ለመሣል የሚያገለግል ቢኾንም እንደ የፊት ለፊቱ የአቋቋም ዘይቤ ብዙ የሚዘወተር አይደለም:: የጎንዮሽ አቋቋም አሣሣል ዘይቤ ሙሉ ለሙሉ እኩይ ባሕርይ ለተላበሱ ( ለምሳሌ:- ሣጥናኤል፣ ሄሮድስ እና በላኤ ሰብእ የመሳሰሉት) እና ከቅድስና ውጭ ያሉ ሰዎች ሁሉ የሚሣሉት በጎንዮሽ የአቋቋም ዓይነት ነው ::

አምስተኛው መለያ ባሕርይ፥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሥዕል ማንነቱን ወይም ምንነቱን የሚገልጽ ገላጭ ጽሑፍ (caption) ያለው መኾኑ ነው:: ይህ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ሁሉም ሥዕሎች ተመሳሳይ በመኾናቸው ነው:: በምዕራቡ ዓለም ልዩ ምልክት (symbol) በመጠቀም በሥዕሉ የተወከለው ቅዱስ ወይም ሰው ማን እንደኾነ ለመለየት የሚያስችል መንገድ ስላላቸው ገላጭ ጽሑፍ ሲጠቀሙ ብዙ አይስተዋልም:: ለምሳሌ ያህል ፥በምዕራቡ ዓለም ክርስቲያናዊ ሥነ ሥዕል ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ቁልፍ የተሰጠው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ከቁጥር 19 እንደተገለጸው ፥ለእርሱ ስለኾነ ቅዱስ ጴጥሮስ የሚሣለው ቁልፉን እንደያዘ በመኾኑ ስለመጽሐፍ ቅዱስ መጠነኛ ዕውቀት ያለው ማንኛውም ሰው ያለገላጭ ጽሁፍ በቀላሉ ሥዕሉ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሆነ ይገነዘባል:: በእኛ አገር ግን ይህ ብዙ የተለመደ የአሣሣል ዘይቤ አይደለም::



www.ethiopianorthodox.org

ሁለት ዐይነት ገላጭ ጽሑፎች ሲኖሩ እነርሱም፥ ማንነት ገላጭ (identity caption) እና ጭብጥ ገላጭ (thematic caption) ይባላሉ:: የመጀመሪያው ግራ መጋባትን (ቅዱስ ሚካኤል ነው ወይስ ቅዱስ ገብርኤል የመሳሰሉትን) ለማስቀረት ለእያንዳንዱ ሥዕል የሚሰጥ ገላጭ ጽሑፍ ሲሆን የኋለኛው ደግሞ የሥዕሉ ዋና መልእክት ምን እንደኾነ የሚገልጽ ነው::

መጠን (size) በቤተ ክርስቲያን የአሣሣል ዘይቤ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተዋረድን (hierarchy) ያመለክታል:: ለምሳሌ ያህል፥ ክርስቶስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋራ አብሮ ሲሣል ክርስቶስ በመጠን ደረጃ ጎላ ተደርጎ ሲሣል ሐዋርያት ደግሞ አነስ ተደርገው ይሣላሉ:: ንጉሥ ከነሠራዊቱ በሚሣልበት ጊዜም ያለውን የፖለቲካዊ ሥልጣን በተዋረድ ለማሳየት ንጉሡ ጎላ ተደርጎ ሲሣል ሠራዊቱ ደግሞ አነስ ተደርጎ ይሣላል:: ከመጠን ጋራ ተያይዞ መታየት ያለበት የሥዕሉ የጥራት (quality) ጉዳይ ይኾናል::

መጠኑ ትልቅ የኾነው ሥዕል በጥራት ማለትም በቀለም አጠቃቀም፣በሞዴልና በንጽጽራዊ ምጣኔ (proportion) የተሻለ ጥራት ሲኖረው በሁለተኛ ደረጃ የተሳሉ ሥዕሎች ግን በቀለም፣ በሞዴል እና ምጣኔ አጠቃቀም ረገድ ያላቸው ጥራት ከዋናዎቹ ሥዕሎች ያነስ ኾኖ እናገኘዋለን :: አንዳንድ ጊዜ በአንድ ሥዕል ውስጥ ከአንድ በላይ ሠዓሊ ሊኖር ይችላል ማለትም ዋናው ሠዓሊ (master) እና ሥዕል የሚማር ደቀ መዝሙር (apprentice) :: ኢትዮጵያውያን የሥዕል ተማሪዎች ሥዕል ለመማር መጀመርያ የሚለማመዱት በጥቁር ቀለም ዲያብሎስን በመሣል ነው፣ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ወይም ሠዓሊ የሚለውን ስም የሚያገኙት ደግሞ የቅድስት ሥላሴን ሥዕል በመሣል ነው:: ሥልጠናቸውን ጥቁር ቀለም በመጠቀም በዲያብሎስ የሚጀምሩበት ምክንያት ጥቁር ቀለም እንደ ልብ ስለሚገኝና በልምምድ ወቅትም ሥዕሉ ቢበላሽ እንኳን የሚወክለው ዲያብሎስን በመኾኑ የሚበላሽ ነገር አይኖርም :: የቅድስት ሥላሴን ሥዕል በመሣል መመረቃቸው ወይም የሠዓሊነት ደረጃ መድረሳቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት የማግኘታቸው ምክንያት የቅድስት ሥላሴ ሥዕል በአንድ ቦታ (panel) ላይ ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ( identical figure) የኾኑ ሦስት ሥዕሎችን በትክክል ማስቀመጥን ስለሚጠይቅ ሠዓሊው ምን ያህል ሥራውን በትክክል ጥንቅቅ አድርጎ መሥራት እንደቻለ ስለሚያረጋግጥ ነው::

ሌላው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአሣሣል ዘይቤ ከሌላው ዓለም የክርስትና ሥዕሎች የሚለየው ብርሃንና ጥላ ፈጽሞ የማይጠቀም መኾኑ ነው ፤ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥዕል ትኩረት የሚሰጠው በሥዕሉ አማካይነት ለሚተላለፈው መልእክት እንጂ ለዕውናዊ ውክልና (realism) ትኩረት አይሰጥም:: በርግጥ 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ የልብስ ዕጥፋት (drapery) የሚያመለክቱ ሥዕሎች እንደ ብርሃንና ጥላ ማሳያ ተደርገው ቢቆጠሩም ዋናው ግባቸው ግን ዕጥፋቱን ለማሳየት እንጂ ብርሃንና ጥላ ለማመልከት አልነበረም::

ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ሥዕል ሠዓሊዎች ከሌላው ክርስትያን ዓለም የሚነሱት አርአያና ምሳሌ (model) ቢኖርም በሁሉም ሠዓሊያን ዘንድ ተቀባይነት ያገኘና አንድ ሥዕል ሲሣል በውስጡ ሊያካትታቸው የሚገቡ የሥዕል ጥንቅሮች (figural composition) የሚወስን ስምምነት (convention) ነበራቸው:: ለምሳሌ ክቅድስት ማርያም እና ከሥነ ሥቅለት ሥዕል ምን መካተት እንዳለበት በሌሎቹም እንዲሁ የሚገልፅ ስምምነት ነበራቸው:: ከኢትዮጵያ ኹኔታ ጋራ አብረው የማይሄዱና ትርጉም የሌላ ቸው የውጭ ሥዕሎች ከመጡ ያስወግዳሉ:: ከተ ቀመጠው ስምምነት ውጭ አንድ ሠዓሊ የራሱ የሥዕል ጥንቅር (figural composition) ቢከተል በሌሎች ሠዓሊዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣት ብቻ ሳይኾን እንደ ኑፋቄም ይቆጠርበታል :: ስለዚህ ጥሩ ሠዓሊ ለመኾን በየሥዕላቱ ውስጥ የሚካተ ቱን ጥንቅሮች (figural composition) ለይቶ ማወቅ በጣም ወሳኝ ሥራ ነበር ማለት ይቻላል::

በርግጥ ሥዕላዊ ጥንቅሮች (figural composition) ከውጭ በሚመጡ አዲስ አርኣያ ዎችና ምሳሌዎች (model) ምክንያት ከዘመን ዘመን የሚቀያየር ነው::ይኹንና ከምዕራቡ ዓለም የክርስትና ሥዕሎች ጋር ሲነጻጸር ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የሥዕል ጥንቅሮች (figural composition ) እና የየዘመኑ የአሣሣል ጥበባዊ ዘይቤ (periodic style) ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ነበር:: ለምሳሌ:- ኢትዮጵያ ውስጥ ከ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው የአሣሣል ዘይቤ ጂኦሜትሪክ የአሣሣል ዘይቤ ሲባል ከ17ኛው እስከ 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ደግሞ የጎንደር ዘመን የአሣሣል ዘይቤ እየተባለ ይጠራል::

በላስታ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ ሥዕሎች እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች ሁሉ በሦስት መልክ ተሥለው ይገኛሉ:: እነርሱም የግድግዳ ሥዕሎች (wall painting)፣ የገበታ ሥዕሎች (panel paining or icon) እና በጥንታዊ የብራና መጻሕፍት



www.ethiopianorthodox.org

ሌላው የዘመኑ ድንቅ ፈጠራ ውጤት የመስቀል ሥራ ነው:: የመስቀል ሥራ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊትም ሆነ በአክሱም ዘመንም የነበረ ጥበብ ነው ::የዛግዌ ዘመን የመስቀል ሥራ ልዩ የሚያደርገው መስቀል ከንዋየ ቅዱስነት ባሻገር ሥነ ጥበባዊ ፋይዳው የጎላበት ዘመን ነበር ለማለት ይቻላል::

በአክሱም ዘመን በጣም ጎልቶ የሚታወቀው የመስቀል ዓይነት የ"ተ" ቅርጽ ያለውና የላቲን መስቀል እየተባለ የሚጠራው መስቀል ነው:: ከዛግዌ መስቀል ቅርጽ ውስብስብነት በመነሳት የላቲን መስቀል ብዙ መጠበብን የሚጠይቅ ነበር ለማለት አያስደፍርም:: መስቀል በዛግዌ ዘመን ሥነ ጥበባዊ ፋይዳው እንዲጎላ ያደረገው ነገር ምን ይኾን? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀሬ ሊኾን ይችላል :: ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የዛግዌ ነገሥታት ንግሥናን ከክህነት ጋራ አጣምረው የያዙ ስለነበሩ ለክርስትናው የተለየ ትኩረት ይሰጡ እንደነበር አንዳንድ መዛግብት ያመለክታሉ::

ከዚህ አንጻር ቀርነ በግዕ (the Horn of the Lamb) ወይም የዛግዌ መስቀል በመባል የሚታወቀው የመስቀል ዐይነት በዚሁ ዘመን የተሠራ የፈጠራ ውጤት ነው:: በጉ የጌታችን መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወይም የተሠዋዉ በግ ምሳሌ ነው:: ከዛግዌ ዘመን በፊት ማለትም በአክሱም ዘመንም መስቀል የክርስትና ምልክት ኾኖ ያገለግል ነበር :: ኾኖም አገልግሎቱ እንደ ዛግዌ ዘመን ሰፊ አልነበረም:: በአክሱም ዘመን መስቀል ይበልጥ ይዘወተር የነበረው በባሕታውያን ነበር የሚል አስተያየት አለ:: በዛግዌ ዘመን ግን በክርስትና ተከታዮች ዘንድ በስፋት መጠቀም የተጀመረበትና በተለይም መስቀል ለአንገት ጌጥነት (ቀደም ሲልም የነበረ ቢኾንም) በስፋት መዋል መጀመሩ ልዩ ያደርገዋል::

በዘመኑ ለመስቀል አጠቃቀም መስፋፋት ምክንያቶች ናቸው የተባሉ ሦስት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: የመጀመሪያው ከላይ እንደተጠቀሰው መስቀል በስፋት ለጌጥነት መዋል መጀመሩ ነው:: ሁለተኛ ው መስቀሎቹ ይሠሩ የነበረው ከወርቅና ብር ስለነበር በማኅበረሰቡ ዘንድ እንደ ሀብት ክምችት መግለጫነት መዋላቸው ነው:: ሦስተኛው ከላይ እንደተጠቀሰው የመስቀል ሃይማኖታዊ ፋይዳ ወይም መስቀል የክርስትና ምልክት ተደርጎ በአማኞች ዘንድ በመወሰዱ ለመስቀል ሥራ መስፋፋት ዐይነተኛ ሚና ነበረው:: ቀደም ሲል የተጠቀሰው ቀርነ በግዕ ወይም የዛግዌ መስቀል የመፆር መስቀል ነው:: ይህ ዐይነቱ መስቀል ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ በሚደረጉ ዐበይት ክብረ በዓላትና አገልግሎቶች ላይ ጥቅም ላይ የሚውል የመስቀል ዐይነት ነው::

በዛግዌ ዘመን መስቀል ልዩ ሥፍራ እንደነበረው ይታወቃል:: ለአብነትም ያኽል:- አንዱ ቤተ መቅደስ በራሱ በመስቀል ስም ቤተ መስቀል ተብሎ መሰየሙ፣ ዝነኛውና ታዋቂው የቤተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በመስቀል ቅርጽ በልዩ ጥበብ መሠራቱ ዋና ማሳያ ነው:: የብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያን በሮቻቸው በልዩ ጥበብ በተሠሩ መስቀሎች ማጌጣቸውን ስንመለከት፣ የንጉሥ ላሊበላ የንግሥና ስሙ ገብረ መስቀል መሆኑና የንግሥቲቱ ስም መስቀል ክብራ ተብሎ መሰየሙ እንደ ተጨማሪ አስረጂ ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ከዚህ በተጨማሪ መስቀል በቅዱስ ላሊበላ ዘመን ልዩ ቦታ እንደነበረው ማሳየው በዘመኑ በታነጹት ውቅር አብያተ ክርትያናቱ 13 ዓይነት መስቀል ቅርጽ በበሮቹና መስኮቶቹ ላይ ተቀርጾ ይገኛል::

ለማጠቃለል :- የዛግዌ ዘመን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መገለጫ የኾኑ ድንቅና ብርቅ የፈጠራ ውጤቶች የተመዘገቡበት ወርቃማ ዘመን ነበር:: ከኢትዮጵያ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቅርስ ከኾኑት ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በተጨማሪ የዘመኑን ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ኹኔታን የሚገልጹ የሥዕል፣ የመስቀልና የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች የታዩበትም ነበር:: እነዚህ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አገራዊና ዓለምአቀፋዊ ቅርሶች የአገርና የትውልድ ምልክት ናቸው:: ለምሳሌ :- የቤተ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ፎቶግራፍ ወይም ምስል በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኀን የሚመለከት ሰው በሐሳቡ ቀድሞ የሚመጣው ሀገሩ ኢትዮጵያ ነች፤ ከዚያም አልፎ ደግሞ የዛግዌን ዘመን ሥልጣኔ ማዘከሩ አይቀርም:: ስለኾነም እኒህ ዘርፈ ብዙ መልክ እና ፋይዳ ያላቸውን የክርስትና መድበለ ጥበባት የየዘመኑ ትውልድ ሊያውቃቸው፣ ሊያጠናቸው ብሎም ሊከባከባቸው ይገባል::

<u>*የመረጃ ምንጮች*</u>


- Di Salvo, Mario. *Crosses of Ethiopia: The Signs of Faith, Evolution and Form*. Milan: Skira, 2006.
- Heldman, E. Marilyn. " Minatures of the Gospels of Prince Zir Ganela , An Ethiopic manuscript dated A.D. 1400/01 " Ph. Dissertation , Washington University , 1972.
- Heldman, E. Marilyn. "The Zagwe Dynasty: 1137-1270)" in Roderick Grierson (ed.) *African Zion: The Sacred Art of Ethiopia.* Fort Worth: Inter Cultra Inc., 1993, pp. 133-139.
- Mengistu Gobezie. *Lalibela: A Museum of Living Rocks*. Addis Ababa: Master Printing Press, 2012.
- Playne, Beatrice. " Reflections on the Decoration of Bieta Mariam, Lalibela" in *Proceedings of the First International Conference on the History of Ethiopian Art* . London: The Pindar Press, 1989, pp. 1-4.
- Taddesse Tamrat . *Church and State in Ethiopia,1270-1527*. Oxford: 1972.




www.ethiopianorthodox.org



# 15. ሕንጻ ላሊበላ የኢትዮጵያ ወርቃማ ሥልጣኔ

በዓለሙ ኃይሉ

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ ጮራ ከፈነጠቀባቸው ሀገሮች ጎራ ትፈረጃለች፡፡ ረጅም የታሪክ ዘመን ካላቸው ግዛቶች ጋርም ትመደባለች፡፡ገና ጨለማና ብዙውም እንዳን ቀላፋ በነበረበት ዘመን ማለት ይቻላል ቀድማ ነቅታ አግራሞትና አድናቆት የተሰ ጣቸው ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አመጣሽ ቅርሶች አበርክታለች፤ አክብሮትና ባርኮት የተቸራቸው የባህል ውርሶች አምርታለች፤ ውብና ማራኪ የሆኑ የወግ አሻራዎች፣ አቅር ባለች፤ ዕፁብ ድንቅ የተሰኙ ሐውልቶችና ሕንጻዎች ሠርታለች፤ በዚህና በመሳሰለውም ስሟን አስጠርታለች፤ አንቱም ተሰኝታለች፤ በርካታዎችንም አስደንቃለች፤ ብዙዎችንም አስገርማለች፡፡

ኢትዮጵያ በጥንታዊ ሥልጣኔ መጥቃ፣ በአኩሪ ታሪክ ደምቃ፣ በረጅም የነጻነት ዘመን ተጠብቃና በተደናቂ ጀግንነት ታውቃ መኖሯን እኛ ተወላጆቿ ብቻ ሳይሆን ጠላቶቿ ሳይቀሩ መመስከራቸውን ታሪክ ያረጋገጠው ሀቅ ነው፡፡

ፋሽስት ኢትዮጵያን ለመውረር በተነሣበት ዘመን በአውሮፓ በጋዜጣና በሬዲዮ ይነዛው በነበረው የጠላት ወሬ ፋሽስት የወረራ ሥራውን በኢትዮጵያ ላይ ቢፈጽምም ሥልጣኔን ላገሪቱ ለመስጠት በማሰብ ነው ብሎ ለማሳመን ይሞክር ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ መሠረት የሌለው አሳብ መሆኑን እያሳሰቡ ብዙ ሊቃውንት ተቃውመውታል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ፒየር አሊፕ የተባለው የፈረንሳይ ደራሲ "ስለሥልጣኔ ጉዳይ በውነት ልንከራከር የምንፈልግ ከሆንን ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ካውሮፓ አገሮች የብዙ ዘመን ቀደምትነት ያላት መሆኗን ልንዘነጋው አይገባም" (የጥንታዊ ታሪክ ቅርስ አጠባበቅ መግለጫ፣ ገጽ 1) ሲል ተገቢ የሆነውን መልስ ሰጥቷል፡፡

የጀግንነት ጉዳይ ከተነሣም አንድ ነገር እንበልና ወደሌላው ጉዳዮችን እንለፍ፡፡ እንደሚታወቀው በዐድዋው ጦርነት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ፣ መሣፍንቱና መኳንንቱ፣ እንደቀትር ንብ ካልነደፉ የማያርፉት፣ እንደተቆጣ ነበር እየተወረወሩ እንደ እሳት ከሚንቀለቀለው የጦርነት ቋያ ውስጥ የሚማገዱት የኢትዮጵያ ጌጥ፣ የታሪኳ ፈርጥ የሆኑት ኢትዮጵያውያን በዘመናዊ መሣሪያው ተመክቶ የመጣውን ወራሪ ሠራዊት ድል በመቱት ጊዜ በጦርነቱ ላይ በጋዜጠኛነትና በጆሌኔት የነበረው ኢቼሊ-ቦዚኒ የተባለ ኢጣልያዊ "የአድዋው ጦርነት" በሚል ከጻፈው ሲቆነጠርለት "ለመሸነፋችን ሌላው ምክንያት ኢትዮጵያውያን በሞራልና በወኔ በመዋጋታቸው ነው....ሐተታ ማብዛት ምን ያረጋል በሚገባ ተሸንፈናል" ሲል ሰፋ ያለ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ (መነን፣ 1964 ፣6) ይህ ድልም ሃኒባል የአልፕን ተራሮች ዞሮ የኤሮፓን ኃይል ድል ካደረገ ወዲህ በአፍሪካ ታሪክ የመጀመሪያው ድል የመላው ኢትዮጵያውያን ድል መሆኑም ተዘግቧል፡፡ (ዝኒ ከማሁ)

ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት፡፡ የሰው ዘር የትመጣነት ምስጢር የተገለጠባት፣ የሰው ልጅ መጀመሪያ የተፈጠረባት፣ ሕይወት



www.ethiopianorthodox.org



ፐርሺያ (ፋርስ) ዛሬ ኢራን፣ ቻይናና እስያ ትልክ፣ ከሀገራቱም ጋር ትናግድ፣ በቀድሞው ዘመንም ከአሁኑ ይበልጥ ይልቅ የፖለቲካ ተጽዕኖ ታደርግ እንነበረም አይካድም (ቢ.ዳር፣ 1959፡10)

ቅድመ ክርስትና በግሪክ ሥልጣኔ ዘመን በባይዛንታውያንና በመካከለኛው ዘመን ጭምር በባህልና በኢኮኖሚው በዚያን ጊዜ ገና ካልታወቁት ከአሜሪካና ሰሜን አውሮፖች ይልቅ ቀድማ የበለፀገች እንደነበረም አሌ አይባልም (ዝኒ ከማሁ)

ጥንት የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ኃይል የደረጀና ያየለ በመሆኑ ወዳጅነቱን እንጂ ጠላትነቱ የሚፈለግ አልነበረም፡፡ የበለፀገ፣ የራሱን ገንዘብ ያስቀረፀ፣ አራትና አምስት ፎቆች የነበሯቸው ሐውልቶች የፈጠረ፣ በሥነ ጽሑፍ የዳበረ፣ በፊደልና በአኃዝ የከበረ፣ ሥሩ የጠለቀ ክርስትና የተስፋፋበት፣ ጥዑም የሆነ ባለምልክት (Nota) ዜማ ያበበበት፣ ኢትዮጵያም ከዓለም የመጀመሪያዋ የሙዚቃ ኖታ ፈጣሪ ሀገር የተባለችበት ጊዜም ነበር፡፡ በረቀቀ ዘዴ ከአንድ ድንጋይ ተቀርፀው የተሠሩ የአክሱም ሐውልቶች ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ቀዋሚ እማኞቻችን ናቸው፡፡

በዚያን ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያውያን በኪነሕንጻ ምን ያህል መጥቀውና በክርስቶስ ፍቅርስ የቱን ያህል ጠልቀው ገብተው እንደነበር የሚያስረዳው ከአገራቸው አልፈው ተርፈው በየመን ሰንዓ (ሀገረ ናግራን) ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን ከመስበካቸውም በላይ ከጥሩ እንጨት፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከወርቅና፣ ከብር የተጌጠ፣ በዕንቁ የተንቆጠቆጠ፣ በመስቀልና በልዩ ልዩ ጌጥ ያሸበረቀ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው እንደነበረ ስናነብ ነው፡፡ ይህን ሀቅ ኢትዮጵያውኑ ብቻ ሳይሆኑ የራሳቸው የዐረብ አገር ጸሐፊዎች ሳይቀሩ በውበቱ ተወዳዳሪ አልነበረውም ሲሉ መስክረውለታል፡፡

ወደ አገራችን ስንመለስ ደግሞ በአክሱም ዘመን የተጀመረው የሕንፃ ጥበብ አድጎና ተመንድጎ ከፍተኛ እመርታ የደረሰበትን የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤትም ዕፁብ ድንቅ የተሰኘበትን ሕንጻ ላሊበላን እናገኛለን፡፡

## ሕንጻ ላሊበላ

ቅዱስ ላሊበላ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን ጭምር ልዩ ሥፍራ ከሚያ ሰጧትና ከሚያኮሯት፣ በዓለም መድረክም ከሚያሳውቋት፣ ጥቁር ሕዝብም ለካ እንደዚህ ያለ የፈጠራ ሥራ ማከናወን ይችልበታልን? ከሚያስብሏት የቅርስ ሙዚየማት መካከል ዋናውና በዓለም የታወቁ በርካታ ነገሥታት መናገሻ ከተማ የነበረ ታሪካዊ መካን ነው፡፡

በውስጡ ግሩምና ድንቅ የሚባሉት ቃላት የማይገልጽዋቸው ከልበ ምድር ውስጥ ከተገኘ አንድ ንጥፍ ዐለት ድንጋይ ልዩ በሆነ ጥበብ ተፈልፍለውና ተቀርፀው የታነጹትን ዐሥራ አንድ አብያተ ክርስቲያናት አቅፎ የያዘው ፣ በሥነ ጥበባዊ ይዘቱ ፣ በአሠራር ጥራቱና ዐይንን በሚስብ ውበቱ የታወቀው የቅዱስ ላሊበላ ግብረ ሕንጻ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ምን ያህል የሥልጣኔ ፀሐይ ወጥቶ፣ የቱንስ ያህል የጥበብ አበባ ፈክቶ እንደነበር የሚያዘክር ቀዋሚ ምስክር ነው፡፡ ቅዱስ ላሊበላ ያነጻቸው በላሊበላ ከተማ ብቻ ከአንድ አለት የተፈለፈሉ ፲፩ ውቅር አብያተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያናት ሲኖሩ እነሱም በሶስት ምድብ ይከፈላሉ፡፡ የመጀመርያው ምድብ ቤተ ማርያም፣ ቤተመድኃኒዓለም፣ ቤተ ጎለጎታ፣ ደብረሲና፣ ቤተ ደናግል እና ቤተ መስቀልን ሲይዝ፣ ሁለተኛው ምደብ ቤተ ገብርኤል፣ ቤተ አባ ሊባኖስ፣ ቤተ መርቆሬዎስ እና ቤተ አማኑኤል፣ በሦስተኛ ምድብ ደግሞ ቤተ ጊዮርጊስ ይገኛል፡፡

ሕንጻ ላሊበላ ታይቶ አይጠገብም፣ "ሞት ሕንጻ ላሊበላ ኩለሄ እንግዳ" ሲል ኢትዮጵያዊው የቅኔ ሊቅ የተቀኘውም ስለዚህ ነው፡፡ ሞት ጧት ሰምተውት ማታ፣ ማታ ሰምተውት ጧት፣ ዛሬ ሰምተውት ነገ፣ ነገ ሰምተውት ከነገ ወዲያ አዲስ (ሁልጊዜ እንግዳ) እንደሚሆን ሕንጻ ላሊበላም ዛሬ አይተውት ነገ፣ ነገ አይተውት ከነገወዲያ ቢያዩት አይለምዱትም ሁሌ አዲስ ሁሌ እንግዳ ይሆንበታል ለማለት፡፡

ኀረ እንደምን አርጎ ሠራው
ኀረ እንደምን አርጎ አነጸው
ለመጥረቢያው እንኳ እጀታ የለው
ዐይኔ ዓለም አየ እግሬ ደርሶ
ዐይኔ ዓለም አየ እግሬ ደርሶ
የድንጋይ ወጋግራ የድንጋይ ምሰሶ

እያለ የልደት ሳሚ (ተሳላሚ) ምእመን በአራራይ ዜማ የሚዘምረውም ይህ አግራሞት በሚፈጥርበት ከፍተኛ ስሜትና አድናቆት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

የቅዱስ ላሊበላ ግብረ ሕንጻዎች የጎብኚዎችን ቀልብ ይስባሉ፣ የተመልካችን ልቡና ይሰርቃሉ፣ የቱሪስቶችን ኅሊና ያማልላሉ፣ የጠቢባንን ዐይን ይማርካሉ፡፡ በዓለም ተወዳዳሪ አልተገኘላቸውም፤ ተመሳሳይም አልተፈጠረላቸውም፡፡ ይህንንም ሀቅ በ፲፭፻፲፪ ዓ.ም (እ.ኤ.አ. በ1520) ወደ ኢትዮጵያ የመጣውና ቅዱስ ላሊበላንም በመጎብኘት የመጀመሪያው አውሮፓዊ ነው የሚባለው ፍራንሲስኮ አልባሬዝ፣ ስለ ቅርሶቹ በብዙ ካተተ በኋላ በመጨረሻ "ስለ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሥራ ብዙ በጽፍም የሚያምነኝ ሰው መኖሩ በጣም ያስጨንቀኛል፣ ያሳስበኛልም፣ እስካሁን ያልኩትንም እንኳ ቢሆን ውሸት ነው ነው የሚሉኝ፡፡ ነገር ግን የጻፍኩት በሙሉ እውነት ለመሆኑ በኃያሉ እግዚአብሔር ስም እምላለሁ እንዲያውም ከዚህ በላይ ማለት ይቻል ነበር ሆኖም ስሜ በቀጣፊነት እንዳይነሳ እሰጋለሁ…ይህን የሚመስል በዓም እንደማ ይገኛኝም እገልጻለሁ" በማለት አድናቆቱን ገልጧል፡፡ እባካችሁ እመኑኝ እንዲህ ያለ ሕንጻ በየትም ዓለም አይገኝም በማለት የጻፈውን እንዲቀበሉለት እየተማፀነ፣ እየማለና እየተገዘተ ለዓለም አስተዋውቆታል፡፡ ሌሎችም ፰ኛው፣ ሌሎች ደግሞ ፱ኛው የዓለም አስደናቂ ነገር ብለው ሰይመውታል፡፡ "አስደናቂ የሚል ቃልና ሥራ በዓለም ቢጠፋ በላሊበላ ብቻ ሊገኝ እንደሚችል" የጻፉም አሉ፡፡

ስለቅዱስ ላሊበላ የጻፉትን አንዳንድ የውጭ ሀገር ሊቃውንት ስም ለማወቅ የፈለገም ሮሀፍ የተባለውን አውሮፓውዊ ጎብኚ ጨምሮ ሞርቲዶላ ካርቴን፣ ቢደርን፣ ቢንቺባሪያን፣ ገርስተርን ወዘተ ማግኘት ይችላል፡፡ ዛሬም ሕንጻዎቹን ጎብኝተው ተገርመውና ተደንቀው አልወጣላቸው ሲል "incredible:- unbelievable:- የማይታመን" እያሉ ገና ሀገራቸው ሳሉ እንደተመኙት ሳይጠግቡት ሰዓት እያጠራቸው ያለውድ



www.ethiopianorthodox.org



በግድ ትተው የሚወጡት ቱሪስቶች አያሌ ናቸው፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በቅዱስ ላሊበላ ዲያቆን እያለ (ከ፰ ዓመት በፊት) አንድ የሶብዮት ሕብረት ፓትርያርክ ሕንጻዎቹን ጎብኝተው ሲያጠናቅቁ አቀባበል ላደረጉላቸው የላስታ ቅዱስ ላሊበላ ኅብረተሰብ "ኢትዮጵያውያን በዚህ ሕንጻችሁ ብቻ እንደኳን ዓለምን አሸንፋችሁታል" ብለው በተመስጦ መናገራቸውን ያስታውሳል፡፡ ያኔ ሉሲ ገና ያልተገኘችበት ዘመን ስለነበር ስለርሷ ሊቀ ጳጳሱ ምንም ሊሉ ባይችሉም ግን እነአክሱም፣ ጎንደር፣ ሀረር፣ አሏችሁ፣ ሌላ ሌላ አስደናቂ ታሪክና ባህል አላችሁ ግን በላሊበላ ብቻ እንኳ ቢሆን ዓለምን ትበልጣላችሁ ማለታቸውን እንደሆነ አድርጎ ይህ ጸሐፊ ተረድቶታል፡፡

ስለ ቅዱስ ላሊበላ ግብረ ሕንጻ በጽሑፍም ሆነ በቃል ለማስረዳት መሞከር ዐባይን በጭልፋ ዓይነት ነው የሚሆነው፡፡ በተለይም በእንደዚህ ዓይነቱ ደካማ ብዕር ለመግለጽ መሞከር "መካነ ቅርሱን በአካል ተገኝተው ለተመለከቱ በአእምሯቸው የቀረ ፁትን መልካም ምስል ማደብዘዝ፣ ገና ለሚጎ በኙትም ስለሕንጻዎቹ ሊኖራቸው የሚገባ ውን ሃይማኖታዊ ትስስርና ምልከታ ማሳነስ" እንዳይሆን ጸሐፊው ይሰጋል፡፡

እንኳን ይህ ጸሐፊ፣ ስለ ቅዱስ ላሊበላና ስለ ሕንጻዎቹ የጻፈው የገድለ ላሊበላ ደራሲም ቢሆን የሚበቃውን ያህል ቃላትና ሐሳብ እንዳላገኘ በሚጥምና ውብ በሆነ ቋንቋ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡

"የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ሥራ መናገር በምን እንደበት እንችላለን? የውስ ጣቸውንስ እንተወውና የቅጽራቸውን ሥራ እንኳ መናገር አንችልም፤ ያየም በማየት አይጠግብም በማድነቅም ልቡ አርፎ ለማውጠንጠን አይችልም፤ ታሪኩን ይቆጥር ዘንድ ለሰው የማይቻለው በላሊበላ ድንቅ የሆነ ታሪክ ተሠርቷልና በላሊበላም እጇ የተሠሩትን አብያተ ክርስቲያናት ሕንጻ ሥራ ያይ ዘንድ የሚወድ ሰው ቢኖር ይምጣ ባይኖቹም ይይ፤

"እንደ ሙሴ ድንኳን የላሊበላ አዳራሾች የሚያረጁ አይደሉምና ወይም እንደሰሎሞን አዳራሾች ጠላቶች የሚያፈርሱት አይደለምና፡፡ የላሊበላ (ገብረ መስቀል) አዳራሾችስ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በምድር ላይ እስክትታይ ድረስ አይነዋወጡም አይጠፉምም፡፡ ጴጥሮስና ጳውሎስ ከመምህራቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደሰም አለምልመው በሦስት ድንጋዮች የቅድስት ድንግልን አዳራሽ ሕንጻ ጨረሱ ላሊበላም እንደዚሁ ጸጋ እግዚአብሔር እየረዳው ካንድ አለት ድንጋይ ዐሥር አብያተ ክርስቲያናት ሠራ ጴጥሮስና ጳውሎስ ደግሞ ካንድ ድንጋይ ላይ አብያተ ክርስቲያናት ሠሩ፡፡ ሥራቸው ግን የጣራው እንጨት በገመድ የተታታ፣ ግድግዳውም የእንጨት ነው ምርጊቱም ጭቃ፣ ምሰሶዎችም እንጨቶች ናቸው፤

"ላሊበላ ግን ካንድ አለት ደንጋይ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሲሠራ ለግድግዳቸው እንጨት፣ ለምርጊታቸው ጭቃ፣ ለጣራቸው ባጥ፣ እንጨትና የገመድ ትት፣ ለክዳናቸውም የሰንበሌጥ ሣር የላቸውም፡፡ የአሠራራቸውም ሁኔታ ብዙ ስለሆነ ሥራቸውን ሁሉ በየመልኩ በየዓይነቱ ዘርዝረን ልንናገር አንችልም" በማለት ተናግሮታል፡፡

በመጨረሻም "ስለዚህ ድንቅ ነገር ሰው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ካንዲት ድንጋይ



www.ethiopianorthodox.org

የተሠሩትን የነዚህን አብያተ ክርስቲያን ዜና ሰምቶ ቅድስት ወደሆነችው ወደ "ሮሀ" አገር ያልደረሰና ይህንን ያላየ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ያይ ዘንድ የማይወድ ሰው ይመስላል" ይላል ደራሲው ከዛሬ ፰፻ ዓመት በፊት ሲጽፍ። ( የዐፄ ላሊበላ ገድል፡ 1952፡ ገጽ 49-50፡ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ፡ 2003፡ ገጽ 267 -268)

የመልክአ ላሊበላ ደራሲም ነግሥ ላይ "ሰብአግብጽ ወሮምለዕበየ ንግሡ ሰገዱ፤ ኩሎሙ ክርስቲያን መቃብሪሁ ዘያዱ፤ ዕሴተበረከት ይንሥኡ እምቅድስት ዐጸዱ" "ሰላም ለላሊበላ ብእሲ አምላክ ፍጹም፡ በእደዊሁ ተሐንጸ ዐሥርቱ ኤላም፡ ይትጋብኡ ውስቴታ አጽናፈ ኩሉ ዐለም..." በማለት አውሮፓና መላው ዓለም ወደ ቅዱስ ላሊበላ ሕንጻ መጥቶ፣ ጎብኝቶ፣ ሰግዶ፡ ገጸ በረከት አቅርቦ፣ እርሱም በረከት ተቀብሎና ተባርኮ እንደሚመለስ ተንብዮአል። እነሆ ትንቢቱ ተፈጽሞ ዓለም ሲጎበኘው፡ ተሳላሚ ሲመለከተው፣ ቱሪስት ሲጎርፍ፤ጎብኚ ሲርመሰመስ ይታያል።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለ ቅዱስ ላሊበላ ግብረ ሕንጻ ለመጻፍ ብሩኅ ኀሊና ላላቸውና የድርሰት ተዋሕቦ ለተሰጣቸው ሊቃውንት መተው ይቀላል። ነገር ግን መካነ ቅርሱን አስመልክቶ አንዳንድ አስተያየት ቢሰጥ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይወዳል። ይኸውም ስለሕንጻዎቹ ዘላቂነት፣ ስለጥበቃቸው አሳሳቢነትና ስለአየያዛቸው እንዴትነት ነው።

## የሕንጻዎቹ ሁኔታ

ሰላም በላዩ ላይ ያለበት ጻድቁ ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ላሊበላ፡ በምክርና በጥበብ፡ በትምህርትና በዕውቀት፡ በማስተዋልና በትእግስት ባለጸጋ የሆነው፣ በውበትና በመንፈሰ እግዚአብሔር የተመላው ቅዱስ ላሊበላ፤ ገና ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ እንደነ ኤርምያስ የተመረጠው፣ እግዚአብሔርን ፈሪ፡ ሰውን አክባሪ፡ ንቁ ሠራተኛ ፍጹም ጸሎተኛ፣ ጥበቅ ጾመኛ የነበረው ሐናጼ መቅደስ ላሊበላ፤ የወጣትነት ዘመኑን ባልባሌ ሳይሆን በቁም ነገረኝነት፣ በተግባር፣ በመማር፡ ሰውን በመታዘዝ ፣ እግዚአብሔርን በማመን፡ በንጽሕና ፣ በቅድስና ሕይወቱን በመጠበቅ ያሳለፈው ቅዱስ ላሊበላ፤ ከግርማውና ከሥራው፣ ከውበቱና ከዕውቀቱ፣ እንደጨው ከተቀመመ ንግግሩና ከመልካም አነዋወሩ፣ ከጥሩ ሰውነቱና ከመንፈሳዊ ሕይወቱ፣ ከትሕትናውና ለጋስነቱ፣ ከኢአድላዊነቱና ለድሃ አሳቢነቱ የተነሣ ሕዝቡ ሁሉ ይነግሥለት ዘንድ ይመኝለት የነበረው ዐፄ ላሊበላ የዛሬ ፱፻ ዓመት ገዳማ የማንንም የውጭ ሀገር ብድርና ርዳታ ሳይፈልግ የሀገር ውስጥ የሕንጻ ጠበብትን አሰባስቦ፣ ንጉሥነኝና ያሻየን ላድርግ ሳይል ቀይት ከምትባል ባለባት በወርቁ ቦታውን ገዝቶ፣ በሥራው ለተሳተፉ ሁሉ ዋጋቸውን ከፍሎ የሠራልን ሕንጻዎች እስከ ዛሬ ድረስ በምግበ ነፍስም ሆነ በምግበ ሥጋ ሲጠቅሙን፣ ስንገለገል ባቸውና ሲያገለግሉን ኖረዋል። ግን ይህ ነገር እስከመቼ ይቀጥላል? አይታወቅም። እንደ ሚታየው ከሆነ አሁን አሁን በሰው ሠራሽና



www.ethiopianorthodox.org

ጀምረዋል፡፡ እግዚአብሔር መላእክትን ፈጥሮ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸው ሳለ በመለኮትነቱ ማየት ተስኗቸው (መኑ ፈጠረነ፣ መኑ ፈጠረነ" በተባባሉ ጊዜ "እኔ ፈጠርኳችሁ" እሚል አለመኖሩን ተመልክቶ "አነ ፈጠርኩክሙ" ሲል ሊቀ መላእክት የነበረው ሳጥናኤል እንደተናጋረው፣ የፈጣሪን ሥራም እርሱው ሊወስድ እንዳጠረው ሁሉ አንዳንድ የውጭ ሰዎች ያልዋሉበትንና ያልሠሩትን ሕንጻ "እኛ ፈጠርነው ሠራነው" ለማለት እየተደፋፈሩ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ቴምፕለርስ (መቅደሳውያን) በተባሉ አውሮፓውያን አጋዥነት ቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናቱን አሳነጸ የሚለው የዘሳይን ኤንድ ዘሲል ደራሲ ግሩም ሃንኮክ ይገኝበታል፡፡ የራሳችንን አንጡራ ሀብት ለሌሎች ለማስተላለፍ የዳዳውና ኋላ እንዳይታተም የተከለከለው "The Monololithic churches of Lalibela and their Treasures" በሚል ርዕስ የጻፈው ጀክስ መርሲርም ሌላው ነው፡፡ የውጮቹ "ዘር ከልጓም ይስባል" ዓይነት እየሆነባቸው ይሆናል፡፡ የሚገርመውስ የነርሱን ብልጣብል ጥና ዐይን አውጣ አባባል ተከትለን የውጭ እጅ እንዳለበት የምናስተጋባ ያንዳንዶቻችን ኢትዮጵያውያን ጉዳይ፡፡

ለምሳሌ ያህል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥ (ዋዜማ በተባለው መጽሐፋቸው)፣ አቶ ተ/ጻድቅ መኩሪያ (የኢትዮጵያ ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከልብነ ድንግል በሚሰኝ መጽሐ ፋቸው)፣ አቶ ብርሃኑ ድንቄ (በኢትዮጵያ አጭር ታሪክ መጽሐፋቸው) ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ደራስያን ግብጽ ተሰደው የመጡ ግብጾች እጅ እንዳለበት ጽፈዋል፡፡

በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመ ( ተአምረ ኢየሱስ) ንጉሡ (ላሊበላ) ከኢየሩሳሌምና ከግብጽ ሀገር ፭፻ የሚሆኑ ድንጋይ ጠራቢዎችንና አናጺዎችን አስመጥቶ፣ ከሀገር ውስጥም ፭፻ የጌጥ ቅርፅ የሚያወጡ ዐዋቂዎችን ሰብስቦ መሥራቱን መጽሐፉ ከተጻፈበት ዋና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ውጭ ገብቶ ጽፏል፡፡ ፈትፍቷል ቢባልስ ሊያስወቅስ? ኢየሱስ ክርስቶስ ገቢረ ተአምራት ያደረገና ይህም በተአምረ ኢየሱስ የተጻፈ የዛሬ ፪ሺህ ዓመት፣ ቅዱስ ላሊበላ የሕንጻ ገቢረ ተአምር ያደረገ የዛሬ ፱፻ ዓመት፣ ታዲያ ሁለቱን ታሪኮች ምን አገናኝቶ ባንድ መጽሐፍ አዋሐዳቸው? ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ፡፡

ደግሞ ጸሐፍቱ ታላቅ ስህተት ላይ መውደቃቸውንና መሳሳታቸውን የሚያጎላው "ሠሪዎቹን" አንዳንዶቹ ከኢየሩሳሌም ሌሎቹ ከግብፅና ከግሪክ ሲያደርጓቸው የተወሰኑት ደግሞ ከሌሎች ሀገሮች (ከአውሮፓ) እያደረጉ እርስ በርሱ የተደባደበ ታሪክ ተብዬ ነገር ማቅረባቸው ነው፡፡ ቁጥራቸውንም ቢሆን አራምባና ቆቦ ነው የሚያረጓቸው፡፡ በተአምረ ኢየሱስ አምስት መቶ ሲሆኑ፣ ሌሎች እስከ ስልሳ ሺህ ያደርሷቸዋል፡፡ "መጻሕፍትስ ለእመቦን አብትረ እምተዛብጣ በበይናቲሆን" (መጻሕፍት እኮ ዱላ ቢኖራቸው እርስ በርሳቸው በተደባደቡ ነበር) (ጌታቸው፣ 1999፡6) የተበላው ተግባር ላይ መዋል የሚገባውስ እነዚህ መጻሕፍት ላይ ነበር፡፡



በውነቱ ያኔ ያን ያህል ሕዝብ ከግብጽ ወደኢትዮጵያ የሚመጣው በጠቅላላ የግብጽ ሕዝብ ቁጥር ምን ያህል ኖሮ ነው? የላሊበላ ከተማስ ይህን ያህል ቁጥር ያለውና የሚርመሰመስ ሕዝብ ለመሸከም እንዴት ቻለቸው? ዛሬ እንኳ 20ሺ ህዝብ መቻል ቸግሯት እያለ? በላስታ የነበሩ አባቶቻችንና እኛስ ለምን ተዳቅለን በመልክም በቋንቋም ፣ በባህልም ግብጻውያን ሆነን አላረፍነውም? ደግሞስ እንኳን ይህን ያህል አንቱ የተባለ ፕሮጀክት ነድፈውና ሕንጻ አንጸው ቀርቶ ትንሹን ነገር እንኳ (ከጸጉር አሠራር ጀምሮ) ከአፍሪካ ዘርፈው ወስደው የኛ ነው ለማለት የሚቀናቸው የውጭ ሰዎች ለምን የሠራነው እኛ ነን ብለው ያኔውኑ ማስረጃ አቅርበው ለዓለም ሳያስተዋውቁ ቀሩ?

የኛ የሆነውን አንጡራ ሀብታችንን ከኛ ቀምቶ ለሌሎች (ባዕዳን) እንካችሁ ማለት የተገባ ሥራ አይደለም፣ ላም ባልዋለበት ያስብላል፡፡ ያስነቅፋል እንጂ አያስመሰግንም፤ ያዋርዳል እንጂ አያስከብርም፣ ሐሰተኛ እንጂ ሀቀኛ አያስብልም፡፡ "እውነተኛ ታሪክ ለመጻፍ ቀላል አይደለም ፣ የሚከተሉት ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋሉና

1. ተመልካች ልቦና፡- የተደረገውን ለማስተዋል
2. የማያዳላ አእምሮ፡- በተደረገው ለመፍረድ
3. የጠራ ቋንቋ ፡- አንብቦ የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ

"ያገራችን ታሪክ ጸፎች ግን በነዚህ ነገሮች ላይ ኃጢአት ይሰራሉ በትልቅ ነገር ፋንታ ትንሹን ይመለከታሉ ለእውነትም ማድረግን ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠባሉ፡፡ አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየሆን ላንባቢ አይገባም...አድልዎ ይበዛበታል፣ የራሳቸውን እንጂ የሕዝቡን ጥቅም ጉዳት ከቶ አይቋጥሩምና...." ሲሉ ከኢትዮጵያ ቀደምት ዘመናውያን ምሁራን መካከል አንዱ የነበሩት ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ "ዐጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ ገጽ 15" በሚለው መጽሐፋቸው እንደጻፉት ሁሉ አንዳንዶችም በቅዱስ ላሊበላ ታሪክ ላይ ኃጢአት ይሠራሉ፤ በአድልኦ ልባቸውን ያጠባሉ ወዘተ ብንል የሚያስኬደን ይመስለኛል፡፡

ሌላ ሌላው ይቆየንና ነጋድራስ " ተመልካች ልቦና" ያሉትን ብቻ እንኳ ብንይዘው ልብ ብሎ ለተመለከተው በቅዱስ ላሊበላ ሕንጻዎች ሥራ ላይ እንዴት ሊሳሳትና ባለቤትነታቸውን ለውጭ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል?

ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያውያን በሕንጻ ጥበብ ከላሊበላ በፊት ጀምሮ መልካም ተሞክሮ እንደነበራቸው ይታወቃል፡፡ በተግባርም ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በትግራይ ውስጥ ብቻ ከ130 በላይ የሆኑ ውቅር አብያተ መቅደሳት ሲኖሩ በላስታና ዋግም ዕድሜያቸውን ከዐፄ ካሌብ ማለት ሕንጻ ላሊበላ ከመታነጻቸው 500 ና 600 ዓመት በፊት የሚቆጥሩ እነብልባላ ጊዮርጊስን፣ ብልባላ ቂርቆስን፣ ሳርዝና ሚካኤልን፣ እመኪና መድኃኔዓለምን የመሳሰሉ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የታነጹ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ልምድ ስለነበራቸውና በሕንጻ ሥራ የተካኑ ነበሩና ልምዳቸውን የበለጠ በማሻሻል፣ በማዳበርና በማላቅ የቅዱስ ላሊበላን ፍልፍል



www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት መሥራቱ አይከብዳቸውም፣ (በነገራችን ላይ ቅዱስ ላሊበላ በኢትዮጵያ ያነጻቸው ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ብዛት ፸፯ መሆናቸውን አባ ገ/መስቀል ከገድለ ቅዱስ ላሊበላ ባጭሩ በሚለው መጽሐፋቸው ያስረዳሉ፡፡)

የውጭዎቹ ሰዎች ግን እንዲሁ አይደሉም፡ በፍልፍል ሕንጻ ሥራ አልተለማመዱም፣ በሀገራቸው አንድ ፀጥ ፍልፍል ሕንጻ እንኳ ጠርበው ሠርተው አላሳዩም መቼም ሀ ሳይባል ፐ አይባልም፣ ሰው የሌለውንም ሊሰጥ አይችልም፡፡ እናም እንዲሁ በድንገት ብድግ ብለውና አገር አቋርጠው መጥተው የሌላቸውን ዕውቀት ተጠቅመው ይህን የመሰለ ውስብስብ አስተናነጽ ሥርዓት ያለው፣ በሰፊው በልበ ምድር ተነጥፎ የነበረውን አለት ከአናቱ ጀምሮ ወደ መሠረቱ በመውረድ ፈልፍሎ፣ በተለያየ ዲዛይን ያሸበረቀ፣ በሐረግ የተጌጠ፣ በሥዕል የተንቆጠቆጠ፣ ከነውስጥ ለውስጥ መተላለፊያቸው፣ ከበርካታ ዋሻዎቻቸው፣ ከነቤተልሔማቸውና፣ ከነቅድስት፣መቅደስና ማሕሌታቸው ጋር ወዙተ መሥራት እንዴት ተቻላቸው? ልምዱና ጅማሮው ለሌለው እንኳን ዐሥር አዳራሾችና በርካታ ዋሻዎች ቀርቶ አንድ ሙቀጫ ወይም የገበጣ መጫዎቻ እንኳን ለመጥረብ ምን ያህል ያስቸግራል? ነው? ወይስ ከሀገራቸው ድንጋይ ጠፍቶ? ዐለት ታጥቶ እዚህ አገር መጥተው ሠሩ? ኧረ ይኸስ ያስገርማል ብቻ ደግነታቸው አንድ ሰው አንድ ጊዜ እንዳሉት ድንጋዩንም ከውጭ ይዘው መጥተው እዚህ ሠሩት አለማለታቸው፡፡

መቼም ኢትዮጵያንም ሆነ ቅዱስ ላሊበላን ለውጪ ዓለም ለማስተዋወቅ ከኛ ከባለቤቶቹ ይልቅ የውጮቹ ቅድሚያ እንዳላቸው የሚያብል አይገኝም፡፡ በዚህ በኩልም ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፡፡ግን አንዳንድ ነጮች ጥቁር ሕዝብ እንአክሱምንና ላሊበላን የመሳሰሉ የትንግርት ሥራ የፈጠራ ባለቤት ነው ሲሏቸው ለመቀበል ይከብዳቸዋል፡፡ ለጥበብ የተፈጠሩ፣ ለዕውቀት የተጠሩ እነርሱ ብቻ የሆኑ ይመስላቸዋል "በቆሎ ከጤፍ ማሕፀን ዱቄት ይወጣል አይመስለውም" አሉ አበው? ኧኸ ብሎ ላዳመጣቸው የሁሉ ነገር ምንጭ እነርሱ እንደሆኑ ከመናገርኮ አያፍሩም፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎችን "ንግበርና ለይኩን" እያልን ሁሉን የፈጠርን አልፋና ኦሜጋ እኛ ነን አይሉም ብሎ መከራከር አይቻልም፡፡ እነርሱ ቀርቶ "የአፍሪካን ወፎች መዘመር ያስተማሯቸው የአውሮፓ ወፎች ናቸው" ብለው ከመናገር ያልቦዘኑ እንዳሉባቸው ማንበቡን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያስታውሳል፡፡ የ16 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች ዘርዓ ያዕቆብ አክሱማዊና ወልደ ሕይወት እንፍራዛዊ የተጠበቡበትንና የተፈላሰፉበትን ጥልቅ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ የፍልስፍና መጽሐፍ "እይ ምናልባት ኢትዮጵያ ኖረው ግእዝ ተምረው የነበሩ ፈረንጆች የጻፉት የፍልስፍና ዓይነት ይሆናል እንጂ እንዴት የኢትዮጵያውያን ፍልስፍና ሊሆን ይችላል?" ብለው የተከራከሩ ፈረንጆች እንደነበሩ አናስታውስንም? ምስጋና ለእነ ፕሮፌሰር ክላውዴ ሳምነር፣ ዓለማየሁ ሞገስና አስረስ የኔሰውን ለመሳሰሉ ምሁራን ይሁንና፣ እነርሱ

በተጣራ ምርምር ሥራ ሐሳባቸውን አፈረ ሱባቸው እንጂ፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ ላይፈረድባቸው ይችል እንደሆነ እንጂ ይህን የመሳሰለ አስተያየት የሚያቀርቡት የዛሬውን የዝቅተኝነት ኑሯችንንና የጉስቁልና ሕይወታችንን እያዩ ነው፡፡ እናም ኢትዮጵያውያን የነ አክሱም፣ የነላሊበላ፣ የነጎንደር፣የነሐረር፣ የነጢያ ወዘተ ባለቤቶች ናቸው ሲሏቸው ሊቀበሉ ይቸግራቸዋል፡፡ ግን ሥልጣኔ ሊያብብ ሊከስም፣ ሊነግና ሊወድቅ፣ ከፍሊልና ዝቅ ሊል እንደሚችል እነ አሦርን፣ ባቢሎንን፣ ካርታጎንን፣ ፊንቄንና ሚዶንን፣ ፋርስንና ግሪክን፣ የሮም አወዳደቅን ወዘተ ማየት ነበረባቸው፡፡ "ዓለም በድንቁርና ተኮንኖ ሲኖር ብቻዋን በሥልጣኔ ጸድቃ ትኖር ነበር" የተባለላት ግሪክ ሁሉ ነገር ፈርሶ የሆሜር ቅኔ ብቻ ሲቀር "ምስኪኒቱ ግሪክ ከቀሩት የበለጠውን ሥልጣኔዋንና የንግግር ጥበቧን ሳይቀር የሮም ሰው ዘርፎ ሲወስድባት ምነው አላዝን አልተክዝ" ሲል አንድ ታላቅ የነበረ ተወላጇ ማልቀሱ ጥንታዊ ሥልጣኔዋ በመውደሙ አይደለምን? እኛስ እግዚአብሔር ይመስገን ምስክር የሚሆን ሥልጣኔ እስካሁን ፈጽሞ አላሳጣንም፡፡ ያዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከቀድሞዋ ብትለይም አባቶቻችን ግን አርቀው የሚያስቡ፣ ጊዜያቸውን ለፈጠራ ሥራ የሚያውሉና በዕውቀት የበሰሉ እንደነበሩ የማያብለው ታሪካቸው ይናገራል፡፡ ሀገሪቱም የብዙ ነገር ምንጭ፣ የሥልጣኔ ፈርቀዳጅ መሆኗንም ይመሰክራል፡፡

"የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መግሪያዎች" በሚል ርዕስ በጥንታዊ የደአማት- አክሱም ጽሑፎች፣ የዐረብ ሰነዶችና በዘመናዊ የሊንጉስቲክና የፓሊኦንቶሎጂ መረጃዎች ወዘተ መሠረትነት የተጻፈው መጽሐፍ "የኢትዮጵያ ምድር ከሁሉ በፊት የሰው ዘር፣ ቋንቋና ሥልጣኔ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት የሰውና የሥልጣኔ ምንጭና መነሻ ነው" ይላል፡፡

አሁን በቅርቡም ፕሪንስተን ሊትማን በUSA (አሜሪካ) የውጭ ጉዳይ ሚ/እና በዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ያገለገሉ ዲፕሎማት "በኢትዮጵያ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ምርጥ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ማግኘት ይቻላል" ብለዋል፡፡ (ሪፖርተር፣ 24/6/95 ዓ.ም)

"የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች" የሚባለው ዳጎስ ያለ መጽሐፍማ "ዛሬ በዓለም ያሉ ቀደምት ሥራዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ሀብትና ንብረት ናቸው" በማለት ኢትዮጵያ ከውጭ የምትቀበል ሳይሆን ለውጪው ዓለም የምትሰጥ ሀገር መሆኗን ያበሥርና ሲቀጥል "ዛሬ የተገላቢጦሽ ቢሆንም ግብርናን ለዓለም ያስተማረችው ኢትዮጵያ ናት…ጤፍን ለአሜሪካ….መርከብን ለዓለም ያስተዋወቀች ኢትዮጵያ ናት፡፡ 850 ቅ..ል.ክ ሐውልቶችን አቅደውና ነድፈው በሂሳብ ስሌትም ቀምረውና ለክተው ለዓለም ያስተዋወቁ ኢትዮጵያውያን ናቸው" ሲል ያስቀምጠዋል፡፡ ታዲያ እንዲህ በሥልጣኔ ቁንጮ ላይ ተቀምጣ የነበረች ሀገር የቅ.ላሊበላ ሕንጻ ለማሳነጽ የሕንጻ ባለሙያ ከውጭ ልታስመጣ? ሀገሪቱ የነጮችንና የአንዳንድ ሀገሮችን የበላይነት ትቀናቀናለች፣ በሥልጣኔም ትወዳደረናለች ብለው የሰጉ የአንዳንድ ሀገሮች ደራስያንን ሐሳብስ እኛ



www.ethiopianorthodox.org